Technology Service Provided by

_______________ ቀን 2013 ዓ.ም

# ይህ ውል የኪራይ መኪና አገልግሎት ሰጪዎች የትራንስፖርት ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የተደረገ የስምምነት ውል ነው

______________________``

## አንቀጽ አንድ
## ስለ ተዋዋዮች

ይህ ውል **በውል ሰጪ** ሃይብሪድ ዲዛይን ኃ/የተ/የግል ማኅበር (ከዚህ በኋላ **"አቅራቢ" ወይም "ራይድ"** በመባል የሚጠራ) ድርጅት

**አድራሻ፡-** ቦሌ ክፍለ ከተማ ቦሌ መድኃኒዓለም አካባቢ ሸገር ሕንጻ 7ኛ ፎቅ የቢሮ ቁጥር 706

ስልክ፡ + 251 938 48 38 21 ኢ-ሜይል: info@hybriddesignsplc.com

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

እና

**በውል ተቀባይ (ስም):** ______________________________________

የሰሌዳ ቁጥሩ: ____________

የጎን ቁጥሩ: ____________________

የአሽከርካሪ የመንጃ ፍቃድ ቁጥር: _________________________

የሆነ አሽከርካሪ ወይም የኪራይ መኪና ባለንብረት (ከዚህ በኋላ **"አገልግሎት ሰጪ"** በመባል የሚጠራ)

አድራሻ፡- _____________ ክ/ከተማ፣ ____________ ወረዳ:_________ የቤት ቁጥር: _________

ስልክ፡ + 251 ________________ ኢ-ሜይል (ካለ): ____________________

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## አንቀጽ ሁለት
## የውሉ ዓላማ

2.1. የዚህ ውል ዓላማ የትራንስፖርት ቴክኖሎጂ አቅራቢው፣ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ህጋዊ ፍቃድ ተሰጥቷቸው ከሚሰሩ የኪራይ መኪና አገልግሎት አካላት ጋር የጋራ ደንበኞቻቸው በሚፈልጉት መልኩ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ አስተማማኝ፣ ምቹ እና ቀልጣፋ የኪራይ መኪና አገልግሎት፣ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ፣ ቦታ፣ እንዲሁም ርቀት ላይ አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችላቸው የተፈጸመ ሲሆን፤ ደንበኛው የትራንስፖርት ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ እንዲጓጓዝ፣ የኪራይ መኪና አገልግሎት ሰጪውም በቴክኖሎጂው በመታገዝ ለሚያገኛቸው ተጠቃሚዎች በዚህ ውል መሰረት የአገልግሎት ጥራት፣ ደረጃና መመሪያዎችን አክብሮ ለደንበኞች አገልግሎት ለመስጠት በመፈለግ እና ለሚያገኘው የቴክኖሎጂ አገልግሎትም ከዚህ በታች በተመለከተው የገንዘብ ተመን መሠረት ለአገልግሎት አቅራቢው ክፍያ ለመፈጸም በመስማማት ይህንን ስምምነት ተዋውለናል፡፡

## አንቀጽ ሶስት
## የአቅራቢ ግዴታዎች

3.1. ራይድ (RIDE) የተባለ የትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች ለመጥራት እና ለማስተናገድ የሚውሉ የትራንስፖርት ቴክኖሎጂ መተግበሪያ ለአገልግሎት ሰጪ ያቀርባል፣
3.2. በቴክኖሎጂ የተደገፈ የትራንስፖርት አገልግሎትን ለማህበረሰቡ ማስተዋወቅ የሚያስችል የተለያዩ የማስተዋወቂያ ስራዎችን ያከናውናል፣
3.3. አገልግሎት ሰጪው ስራውን እና አገልግሎቱን በመልካም ስነምግባር፣ በተሳካ እና በተሳለጠ መንገድ እንዲሰጡ ይረዳቸው ዘንድ አስፈላጊውን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ የስራ ስነ-ምግባር እና የደንበኛ አያያዝ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በዘርፉ በተመረጡ ባለሞያዎች ስልጠናዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ አራት
## የአገልግሎት ሰጪ ግዴታዎች

4.1 በአቅራቢው የትራንስፖርት መተግበሪያ ቴክኖሎጂ ብቻ የሚቀርብለትን የትራንስፖርት ጥሪ በመቀበል አገልግሎቱን ለተጠቃሚዎች በፍጥነት ያቀርባል፣
4.2 የኪራይ መኪናውን የሚያሽከረክረው ከባለቤቱ ውጭ በተቀጣሪ አሽከርካሪ ከሆነ ይህንን የሚያሳይ ህጋዊ የቅጥር ውል ያቀርባል፣
4.3 በተመዘገበው መኪና አገልግሎቱን ለተጠቃሚዎች በሚሰጥበት በማናቸውም ጊዜ አሽከርካሪው የሚከተሉትን ማከናወን ይጠበቅበታል፡-
   4.3.1 ንፁህ ሸሚዝ እና በደንብ የተተኮሰ ሱሪ መልበስ፣
   4.3.2 የኪራይ መኪናውን ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ጽዳትና ውበት መጠበቅ፣
   4.3.3 ተሳፋሪውን በቅንነት እና ረጋ ባለ መልኩ የማናገር እንዲሁም ማስተናገድ፣
   4.3.4 ተሳፋሪውን ምቾት እና የጋራ ደህንነት በጠበቀ መልኩ በጥንቃቄ ማሽከርከር፣
   4.3.5 ተሳፋሪ ወደ ተሽከርካሪው ከመግባቱ በፊት ደኅንነቱና ምቾቱ የሚጠበቀው ከኋላ ወንበር ሲቀመጥ እንደሆነ በትህትና የማሳሰብ፤ ተሳፋሪው ማሳሰቢያውን ከሰማ በኋላ ከፊት ወንበር ላይ ለመቀመጥ ከመረጠ የተሳፋሪውን ምርጫ መቀበልና፣
   4.3.6 አገልግሎቱን በሚሰጥበት ማናቸውም ጊዜ ተንቀሳቃሽ ስልኩን ተሳፋሪው በቀላሉ ሊያየው በሚችልበት ቦታ በስልክ ማስቀመጫ ላይ ማስቀመጥ፣
   4.3.7 የኪራይ መኪና አገልግሎት በሚሰጥበት በማናቸውም ጊዜ የግል ችግር ለተሳፋሪ ያለማጫወት፣
   4.3.8 በተሳፋሪዎች መካከል ልዩነት ወይም መድሎ ሳያሳድር የተሳፋሪዎቹን ሻንጣ ወይም በተሽከርካሪው ላይ ለመጫን የተፈቀደላቸውን ዕቃ ሲጭኑ በቅንነት የማገዝ፣
   4.3.9 በጉዞ መስመር ላይ ተሳፋሪው ወደሚደርስበት ስፍራ ለመጓዝ ከአንድ በላይ አማራጭ መንገዶች ካሉ ጉዞውን ከመጀመሩ በፊት ተሳፈሪው በየትኛው አማራጭ ሊጓዝ እንደሚፈልግ የመጠየቅ እና ከአማራጭ መንገዶቹ አጭሩን የጉዞ መስመር መርጦ የመጓዝ፣

4.3.10 ተሳፋሪዎቹ አረጋውያን፣ እርጉዝ ሴት፣ ታካሚዎች ወይም አካል ጉዳተኞች ወይም ድጋፍ የሚሹ ማናቸውም ሰዎች ከሆኑ ለመሳፈርም ሆነ ለመውረድ እንደሚመቻቸው ተገቢውን ድጋፍ፣ እንክብካቤና ፍቅር በመለገስ ያለአድሎ ትብብር የመስጠት፣

4.3.11 በዝናብ ወቅት ተሳፈሪው ወደ ተሽከርካሪው ሲገባም ሆነ ሲወርድ ዣንጥላ በመያዝ የማገልገል፣

4.3.12 የኪራይ መኪና አገልግሎት በተጠየቀ በ10 ደቂቃ ውስጥ ወደ ተሳፋሪው የመድረስ፣ ቀድሞ ለተያዙ ትዕዛዞች ከ10 ደቂቃ በፊት ተሳፋሪው ወዳለበት የመድረስ፣ በ10 ደቂቃ ውስጥ ወይም ቀደም ብሎ ተሳፋሪው ወዳለበት ለመድረስ የማያስችል፣ ካቅም በላይ የሆነ እክል ከገጠመው ለራይድ የስልክ ጥሪ ማዕከል የአገልግሎት ለውጡን ቀደም ብሎ ከ20 ደቂቃ በፊት የማሳወቅ እና ወደ ተሳፋሪው ስልክ በመደወል የማሳወቅ እና የመመካከር፣

4.3.13 የኪራይ መኪና አገልግሎት በሚሰጥበት በማናቸውም ጊዜ በጥንቃቄና በትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንቦች በተፈቀደ ሕጋዊ የፍጥነት ወሰን የማሽከርከር፣

4.3.14 ደኅንነቱና ምቾቱ የተጠበቀ የኪራይ መኪና አገልግሎት ለመስጠት በአካልና በመንፈስም ዝግጁ ለመሆን ያስችለው ዘንድ የድካም ስሜት በተሰማው ጊዜ በቂ እረፍት የማድረግ፣

4.3.15 የኪራይ መኪና አገልግሎት በሚሰጥበት በማናቸውም ጊዜ የደኅንነት ቀበቶ (ሲት ቤልት) የማሰር እና ተሳፋሪው በፊተኛው ወንበር ለመቀመጥ ከመረጠ የደኅንነት ቀበቶ (ሲት ቤልት) እንዲያሥር በትህትና የማሳሰብ፣

4.3.16 የኪራይ መኪና  አገልግሎት በሚሰጥበት ማናቸውም ጊዜ በትራፊክ መጨናነቅ፣ ፀባያቸው ወይም ባህሪያቸው የማይስማማ ተሳፋሪዎች በመጫኑ ወይም በሦስተኛ ወገኖች ድርጊት መነሻነት በተሳፋሪዪ እና በእኔ በአሽከርካሪውም መካከል አለመግባባት ወይም የስሜት መጋል ከተከሰተ አለምግባባቱን በሰከነ መንፈስ የመፍታት እና በጊዜው ለጥሪ ማዕከል ማሳወቅ፣

4.3.17 ከአቅራቢው ለሚመጣ ጥሪ የራይድ ቴክኖሎጂ ከሚያሰላው የአገልግሎት ዋጋ በላይ ተሳፋሪን ያለመጠይቅና ያለማስከፈል፣  የቴክኒካል ብልሽት ካጋጠመው ወይም ከተሳፋሪ ቅሬታ ከተነሳ ከማስከፈል በፊት ለጥሪ ማዕከል የማሳወቅ፣

4.3.18 የኪራይ መኪና አገልግሎት በሚሰጥበት ማናቸውም ጊዜ በማሽከርከር አካላዊም ሆነ አዕምሮአዊ ብቃት ወይም በባህሪ ወይም በሁለቱም ላይ ተጽዕኖ ማድርግ ከሚችሉ ማናቸውም የአልኮል መጠጥ፣ ጫት፣ አደንዛዥ ዕጽ ወይም ማናቸውም ነገር ነጻ ሆኖ የመገኘት፣

4.3.19 የኪራይ መኪና  አገልግሎት በሚሰጥበት በማናቸውም ጊዜ ተሳፋሪ የሚወርደው ጨለማ በሆነ አካባቢ ከሆነ የተሽከርካሪን ወይም ሌላ ማቸውም መብራት በማብራት ተሳፋሪ ወደሚገባበት ስፍራ እስኪገባ ቆሞ የመጠበቅ፣

4.3.20 አገልግሎት በሚሰጥበት በማናቸውም ጊዜ ተሽከርካሪን ከማንኛውም መጥፎ ጠረን የጸዳ የማድረግ፣

4.3.21 አገልግሎት በሚሰጥበት ማናቸውም ጊዜ ለሚሰጠው አገልገሎት በተሽከርካሪ ውስጥም ሆነ ውጪ ከራይድ ፈቃድ ያልተሰጣቸውን የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች (አፕሊኬሽንስ) ያለመጠቀም፣

4.3.22 ከአቅራቢው የፅሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ ለሚሰጠው የትራንስፖርት ጥሪ አገልገሎት ከራይድ በተቀበለው ስልክ ላይ ምንም አይነት የቴክኖሎጂ መተግበሪያዎች (አፕሊኬሽንስ) ያለመጫን እና ከራይድ ሥራ ውጪ ያለመጠቀም፣

4.3.23 ከአቅራቢው የፅሁፍ ፈቃድ ሳላገኝ ለሚሰጠው የትራንስፖርት ጥሪ አገልገሎት የግል አካውንት እንዲሁም በራይድ የተመዘገበ ሲም ካርድን ሌላ ሰው እንዲገለገልበት ያለመስጠት፣

4.3.24 የኪራይ መኪና አገልግሎት በሚሰጥበት ማናቸውም ጊዜ የራይድን የቴክኖሎጂ መተግበሪያ (አፕሊኬሽን) መጠቀም ወይም ስልክ መጠቀም ካስፈለገኝ ተሽከርካሪን የማቆም፣

4.3.25 የኪራይ መኪና አገልግሎት በማልሰጥበት ማናቸውም ጊዜ በጉዞ ወቅት የራይድን የቴክኖሎጂ መተግበሪያ (አፕሊኬሽን) 'ከአገልግሎት ውጭ' "Offline" ላይ የማኖር፣

4.3.26 የኪራይ መኪና አገልግሎት በሚሰጥበት ማናቸውም ጊዜ ተሽከርካሪንም ሆነ እራሱ አሽከርካሪውን የሚመለከቱ ማናቸውም ሕጋዊ ሰነዶችን አሟቶ የመገኘት፣

4.3.27 የኪራይ መኪና አገልግሎት በሚሰጥበት ማናቸውም ጊዜ በራይድ የሚወጡትን የሥራ መመሪያዎች የመከታተልና የመተግበር፣

4.3.28 የሚገለገልበት የራይድን የቴክኖሎጂ መተግበሪያ (አፕሊኬሽን) አገልግሎት ካሰባት ቀን ባነሰ ጊዜ ውስጥ ለራይድ የማሳወቅ፣

4.3.29 አገልግሎት የሰጠበትን ቀሪ ሒሳብ አቅራቢው በተጣለው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማወራረድ፣

4.3.30 የሚገለገልበት የአቅራቢ ቴክኖሎጂ መተግበሪያ (አፕሊኬሽን) የተሳሳተ ወይም እላፊ ሂሳብ ከቆጠረ ለራይድ ጥሪ ማዕከል ወዲያውኑ የማሳወቅ፣

4.3.31 የኪራይ መኪና አገልግሎት ለመስጠት ከአቅራቢው የተቀበላቸውን ማናቸውም የቴክኖሎጂ መሣሪያ በጥንቃቄ ለመያዝ፣ ለመገልገልና በራይድ በተጠየቅኩኝ ጊዜ የመመለስ፣

4.3.32 ከአቅራቢው ሠራተኞች ጋር ጥሩ ግንኙነትን የፍጠርና በመግባባት መሥራት፣

4.3.33 የሚገለገልበትን የቴክኖሎጂ መተግበሪያ (አፕሊኬሽን) ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ራይድ መሥሪያ ቤት በመደወል ወይም በአካል በመገኘት የማሳየት እና የማስተካከል፣

4.3.34 የኪራይ መኪና አገልግሎት በሚሰጥበት ማናቸውም ጊዜ በአገሪቱ የሚገኙትን የተለያዩ የወንጀል እና የፍታብሔር ሕግጋት፣ የራይድን መተዳደሪያ ደንብን እንዲሁም ይህንን ውል በመጣስ ለሚጣል ማንኛውም ቅጣት ኃላፊነት የመውሰድ፣ እና

4.3.35 የኪራይ መኪና አገልግሎት በሚሰጥበት ማናቸውም ጊዜ የሚፈጠሩ ማንኛውንም አለመግባባቶችን በሥነ ምግባር፣ በሕግና በደንብ መሠረት የመፍታት ግዴታ አለበት፡፡

4.4 በአሽከርካሪው የራይድ አፕልኬሽን ላይ የተመዘገበን ታርጋ ብቻ የያዘ መኪና እያሽከረከረ የራይድ አገልግሎት ለመስጠት፤ ታርጋ ቁጥሩ አፕልኬሽኑ ላይ በስህተት ከተመዘገበ ወዲያው ለራይድ ጥሪ ማዕከል ለማሳወቅ፡፡

4.5 የተሳፋሪን አንድ ሻንጣ ያለ ክፍያ በነፃ የመጫን ግዴታ አለበት፡፡ ነገር ግን የሻንጣው ብዛት ከ 1 በላይ በሆነ ጊዜ በእያንዳንዱ ሻንጣ ብር 25.00 (ሃያ አምስት ብር) በማስከፈል የሚጭን ይሆናል ፡፡

4.6 የመኪናው ደህንነት መጠበቅ ያስችል ዘንድ በየ 6 ወሩ ራይድ በመደበበት የቁጥጥር ጋራዥ በማቅረብ መኪናውን የማስመርመር ግዴታ አለበት፤

4.7 አገልግሎት ሰጪው በየ3 ወር በአካል የራይድ ጽ/ቤት ቀርቦ አገልግሎት የሚሰጥበትን ሞባይል ለፍተሻ ማቅረብ እና ስልክ ላይ የተለጠፈው ማሳሰብያ እንዲታደስ ማድረግ፡፡

4.8 የሚጠቀምበት የራይድ የግል አካውንት የተጫነበት ስልክ በማናቸዉ ምክንያት ቢጠፋ በራይድ ጽ/ቤት በአካል ቀርቦ በ48 ሰዓት ውስጥ ማሳወቅ አለበት ፡፡

## አንቀጽ አምስት
## የአገልግሎት ክፍያን በተመለከተ

5.1 የኪራይ መኪና አገልግሎት ሰጪው ለደንበኛ አገልግሎት በመስጠት ከሚያገኘው ገቢ ከዚህ በታች በተመለከተው መሰረት ለአቅራቢው ክፍያ የሚፈፅም ይሆናል፡-

5.1.1 አሽከርካሪው በ 1 ወር ውስጥ በጠቅላላ ከ120 በላይ ስራዎችን ካከናወነ በጥቅሉ 12% (10.2% ኮምሽን + 1.8% ተጨማሪ እሴት ታክስ) ይከፍላል፣

5.1.2 አሽከርካሪው በ 1 ወር ውስጥ በጠቅላላ ከ61 እስከ 119 ስራዎችን ካከናወነ በጥቅሉ 15% (12.75% ኮምሽን + 2.25% ተጨማሪ እሴት ታክስ) ይከፍላል፣

5.1.3 አሽከርካሪው በ 1 ወር ውስጥ በጠቅላላ ከ60 በታች ስራዎችን ካከናወነ በጥቅሉ 17% (14.45% ኮምሽን + 2.55% ተጨማሪ እሴት ታክስ) ይከፍላል፣

5.1.4 በወር በጠቅላላው ከ30 በታች ስራዎችን ብቻ ካከናወነ 250.00 ብር የአገልግሎት ክፍያ የሚከፍል ይሆናል።

5.1.5 ድርጅቱ ባዘጋጀው ማንኛውም የእርዳታ ፕሮግራሞች ላይ ልሳተፍ ካልሆነ አስቀድሜ በደብዳቤ የይለፈኝ ማሳሰብያ ልሰጥ

## አንቀጽ ስድስት
## ውሉ ስለሚቋረጥበት ሁኔታና ስለ ቅጣት

6.1 ይህ ውል በሚከተሉት ምክንያቶች ሊቋረጥ ይችላል፡-

6.1.1 የኪራይ መኪና አገልግሎት ሰጪው በዚህ ውል ውስጥ የተጣሉበትን ግዴታዎች ያለበቂ ምክንያት ሳይፈጽም ከቀረ አቅራቢው ይህን የስምምነት ውል ለመሰረዝ ይችላል፣

6.1.2 ተገልጋዮች የኪራይ መኪና አገልግሎት ሰጪውን በተመለከተ ቅሬታ ካቀረቡበት፣ ቴክኖሎጂ አቅራቢው የቀረበውን አቤቱታ በማጣራት ጥፋት ነው ብሎ ካመነበት ያለ ምንም ማስጠንቀቂያ በተናጥል ውሉን ለመሰረዝ ይችላል፣

6.1.3 አቅራቢው በውሉ ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ሳይፈጽም ከቀረ የኪራይ መኪና አገልግሎት ሰጪው ጉድለቱ በአንድ ወር ውስጥ እንዲስተካከልለት በፅሁፍ ጠይቆ ማስተካከያ ካላገኘ ውሉን ማቋረጥ ይችላል፣

6.1.4 አገልግሎት ሰጭ ለአቅራቢው ሳያሳውቅ ያለ በቂ ምክንያት ለአንድ ወር ያህል ምንም ጥሪ ካልተቀበለ አቅራቢው ይህንን ውል በተናጥል መሰረዝ ይችላል፣

6.1.5 ሁለቱም ወገኖች በፅሁፍ በሚፈጽሙት ስምምነት ውሉን ለማቋረጥ ይችላሉ፡፡

6.2 የውሉ ማቋረጥ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ያስከትላል፡-

6.2.1 አገልግሎት ሰጪው በሲስተሙ ላይ ቀሪ ሒሳብ ካለዉ ተመላሽ አይሆንም፣

6.2.2 አገልግሎት ሰጪው ውሉ ከተቋረጠ በኋላ ተመልሶ አገልግሎት መስጠት ቢፈልግ 2,150.00 (ሁለት ሺ አንድ መቶ ሀምሳ ብር) ለውሉ ማደሻ የሚከፍል ይሆናል፡፡

6.3 **ስለ ቅጣት፡-** ከዚህ በላይ ውልን ስለማቋረጥ የተጠቀሰው እና በተለያዩ የትራፊክ ደንቦች እና ህግጋት የተጠቀሱት እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው፡-

6.3.1 የኪራይ መኪና አገልግሎት ሰጪው የመኪናው ባለቤትም ይሁን በእርሱ ስር ተቀጥሮ የሚሰራ አሽከርካሪ ከሆነና ከአቅራቢው የፅሁፍ ፈቃድ ሳያገኝ ለሚሰጠው አገልገሎት ከጥሪ አገልግሎት አቅራቢው የተሰጠውን የጥሪ አገልገሎት መጠቀሚያ የግል አካውንቱን እንዲሁም በራይድ የተመዘገበ ሲም ካርድን ለሌላ ሰው እንዲገለገልበት ሰጥቶ ከተገኘ ወይም ይህንን ቴክኖሎጂ የታርጋ ቁጥሩ በራይድ ባልተመዘገበ መኪና ላይ ሲጠቀም ከተገኘ ለአገልግሎት አቅራቢው የሚከተለውን ቅጣት ለመክፈል ተስማምቷል፡፡

6.3.1.1 አገልግሎት ሰጪው ይህንን ድርጊት ለመጀመሪያ ጊዜ ከፈጸመ ለቴክኖሎጂ አቅራቢው ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታ አለበት፤

6.3.1.2 አገልግሎት ሰጪው ይህንን ድርጊት ለሁለተኛ ጊዜ ሲፈጽም ከተገኘ ለቴክኖሎጂ አቅራቢው ብር 50,000.00 (ሃምሳ ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታ አለበት፤

6.3.1.3 አገልግሎት ሰጪው ይህንን ድርጊት ከሁለት ግዜ በላይ ሲፈጽም ከተገኘ ከላይ በፊደል ለስር የተቀመጠው ቅጣት የሚከፍል ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የቴክኖሎጂ አቅራቢው ደንበኛውን ሙሉ ለሙሉ ከሲስተም በማስወጣት የሚሰርዘው ይሆናል፡፡

6.3.2 የኪራይ አገልግሎት ሰጪው የሚጠቀምበት የራይድ የግል አካውንት የተጫነበት ስልክ በማናቸዉ ምክንያት ቢጠፋና ለራይድ ጽ/ቤት በአካል ቀርቦ በ48 ሰዓት ውስጥ ባለማሳወቁና ይህን አካውንት ሌላ ግለሰብ ሲጠቀምበት ቢገኝ ለቴክኖሎጂ አቅራቢው ብር 25,000.00 (ሃያ አምስት ሺህ ብር) የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

6.3.3 የኪራይ መኪና አገልግሎቱን የሚሰጠው ተቀጣሪ አሽከርካሪ ከሆነ፤ የመኪናው ባለቤት ይህ አሽከርካሪ ከርሱ ጋር ያለው የውል ግንኙነት ሲቋረጥ ውሉ በተቋረጠ በሰባት ቀናት ውስጥ ለቴክኖሎጂ አቅራቢው በማሳወቅ ግለሰቡ ቴክኖሎጂውን እንዳይጠቀምበት እንዲታገግ ማድረግ አለበት፡፡ ነገር ግን የተሽከርካሪው ባለቤት ይህንን ግዴታውን በተጠቀሰው ግዜ ውስጥ ሳይፈጽም እና አሽከርካሪው ቴክኖሎጂውን በሌላ መኪና ሲጠቀም ከተገኘ የመኪናው ባለቤት ለቴክኖሎጂ አቅራቢው ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ለመክፈል ተስማምቷል፡፡

6.3.4 አገልግሎት ሰጪው የቀጠሮ ስራ ተቀብሎ ቦታው ላይ በተቀጠረበት ሰዓት እና ቦታ ሳይገኝ ቢቀር የስራውን ግምት ሒሳብ ለመክፈል ተስማምታል ፡፡

## <u>አንቀጽ ሰባት</u>
## <u>ልዩ ድንጋጌ</u>

ይህ ውል ከተፈጸመ በኋላ ለጋራ ደንበኞቻቸው የሚሰጠውን የትራንስፖርት አገልግሎትን በተመለከተ፣ በተላያዩ ጊዚያት **ከራይድ** ለአገልግሎት ሰጪው የሚላኩ የተለያዩ ደብዳቤዎች፣ መልዕክቶች፣ የሚሰጡ መግለጫዎች እንዲሁም ራይድ በሚጠራው ስብሰባ ላይ የሚተላለፉ የውሳኔ ሃሳቦች፣ ራይድ የሚያወጣው የአሰራር ፖሊሲ መመሪያ በ **8202** የሚላክ የአጭር መልዕክቶች እና የመሳሰሉት የዚህ ውል አካል ተደርገው እንዲቆጠሩ ተዋዋዮቹ በሙሉ ፍቃዳቸው ተስማምተዋል፡፡

# አንቀፅ ስምንት
## ውሉ የሚቆይበት የጊዜ ገደብና የስምምነት ማረጋገጫ

8.1 ይህ የትራንስፖርት አገልግሎትን በትራንስፖርት ቴክኖሎጂ ለመደገፍ የተደረገ የስምምነት ውል በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል በፍ/ሕ/ቁ/1731 መሠረት ሕግ ሆኖ ላልተወሰነ ጊዜ ፀንቶ ይቆያል፡፡

8.2 እኛ የዚህ ውል ተዋዋይ ወገኖች ይህንን ውል አንብበንና የውሉን ይዘት በሚገባ ተረድተን በሙሉ ፍቃዳችን በዚህ ውል በተቀመጡት የስምምነት ነጥቦች ላይ መስማማታችንን በተለመደው ፊርማችን እናረጋግጣለን፡፡

## የተዋዋይ ወገኖችና የምስክሮች ስምና ፊርማ

| የአቅራቢው ተወካይ ፊርማ | የአገልግሎት ሰጪ (ባለንብረት) ፊርማ |
| --- | --- |
| ስም ____________________ | ስም ____________________ |
| ፊርማ ___________________ | ፊርማ ___________________ |
| ቀን _____________________ | ቀን _____________________ |

የኪራይ መኪናው አሽከርካሪ ፊርማ (**መኪናው የሚሽከረከረው ከባለቤቱ ውጪ በሆነ ግዜ ብቻ መፈረም ያለበት**)

ስም ____________________

ፊርማ ___________________ ቀን _____________________

| 1ኛ. ምስክር | 2ኛ. ምስክር |
| --- | --- |
| ስም ____________________ | ስም ____________________ |
| ፊርማ ___________________ | ፊርማ ___________________ |
| ቀን _____________________ | ቀን _____________________ |

እኛ ስማችንና ፊርማችን ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ምስክሮችም ተዋዋይ ወገኖች በዚህ ውል በተገለጹት የስምምነት ነጥቦች ላይ በሙሉ ፈቃዳቸው መስማማታቸውን በፊርማቸው ሲያረጋግጡ የተመለከትን መሆኑን በተለመደው ፊርማችን እናረጋግጣለን፡፡

ይህ ውል ዛሬ _________________ ቀን ________ ዓ.ም አዲስ አበባ ______________ ክ/ከተማ ልዩ ቦታው _________________________ ተፈረመ፡፡